# እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2017 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት ሁለተኛው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላ፡ይ የተሻለ ጥንካሬ የነበራቸው ሲሆን፤ አልፎም አልፎ ወደ መካከለኛው እና ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ተስፋፍቶ ነበር። ከዚህም ጋር በተያያዘ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ለመጥቀስ ያህልም በሲርባአባያ 40.5፣ በቋራ 49.8፣ በማንኩሽ 42.7፣ በአርጆ 36.0፣ በጊንቢ 40.1፣ በነቀምቴ 79.9፣ በአቦቦ 30.0፣ በዳንግላ 42.9፣ በሴሩ 30.8፣ እና በሸርኮሌ 32.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት አብዛኛው ትግራይና አማራ፣ ቤንሻጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ እና ሰሜን ሰማሌ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ምዕራብ ትግራይና አማራ፣ ቤንሻጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ እና ሰሜን ሰማሌ ከ5-191 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-10 ቀናት ያህል ዘንቧል(ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር የምዕራብ ትግራይ ኪስ ቦታዎች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር እና ጥቂት የሰሜን ወሎ ዞን፤ ቤንሻጉል ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ እና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ እና ምስራቅ ሀረርጌ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ እና ከሰማሌ ክልል የጅግጅጋ እና የሽንሌ ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛበታች ዝናብ ነበራቸው(ካርታ 3)።


ካርታ 1    እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     እ.ኤ.አ  ከጁን 11 እስከ 20/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



**ካርታ 3   እ.ኤ.አ  ከጁን 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**




# እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ሁለተኛ የጁን አስር ቀናት በተለይም በምዕራብ አጋማሽና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከእርጥበታማ እስከ በጣም እርጥበታማ የአየር ሁኔታ በስፋት የተስተዋለበት ሲሆን፤ በተጨማሪም በአንዳንድ የመካከለኛውና የምስራቅ ሀረርጌ ኪስ አካባቢዎች ላይ እርጥበታማ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

ይህም ሁኔታ በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት እርካታ መልካም አቅርቦት እንደነበረው መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የነበረው በጣም እርጥበታማ የአየር ሁኔታ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያየዞ በአንዳንድ አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም፤ በዚሁ ጉዳይ ላይ ግን ሪፖርት አልቀረበም፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛውና በሰሜኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት በስፋትም ሆነ በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ በጎ ሚና እንደነበረው ይገመታል፡፡ በአንጻሩም ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ባዘነበለባቸው አካባቢዎች በእርሻ ስራም ሆነ በእንስሳት ልማት ላይ አሉታዊ ሚና ነበረው
(ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

# በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 11-20 ጁን 2017 በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው የአየር ሁኔታ ገፅታን በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራብና በደቡባዊ አጋማሽ አባይ፣ በላይኛው ባሮአኮቦ፣ በላይኛው ኦሞጊቤ እና በአባይ ደቡባዊው ክፍል አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት ነበር። በተጨማሪም እርጥበታማና መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ተፋሰሶች በምዕራባዊ የአገሪቱ ተፋሰሶችና በጥቂት የመካከለኛው ክፍል አካባቢ የሚገኙ ሲሆኑ፤ እነዚህም የተከዜ ምዕራባዊ አጋማሽ ክፍል፣ የታችኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛው ኦሞጊቤ ምስራቃዊ ክፍል፣ የመካከለኛው አባይ፣ ጥቂት የላይኛው አዋሽና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ናቸው። በተቀሩት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተሰተውሏል። በተለይ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የነበረው ደረቅ ሁኔታ ከቀኑ ሙቀት ጋር ተዳምሮ በውሃ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5)።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## ኢ.ኤ.አ. ከጁን 21-30/ 2017 የሚኖረው

## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የጁን ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ እየተጠናከሩ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎችን የሚያዳርሱበት ጊዜ ነው።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የባህርና የከባቢ አየር ክስተቶች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ አርሲና ባሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፤ ከትግራይ የክልሉ ሁሉም ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታና የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል። ከዚህም ሌላ የሰሜን ሸዋ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ እንዲሁም አጎራባች የአፋር ዞን 3 እና 5 በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## ኢ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው ሦስተኛው የጁን አስር ቀናት ሰፊ የቦታ ሽፋን ያለው የእርጥበት ስርጭት ሊኖር እንደሚችል ግንዛቤ መውሰድ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በትንበያው በተጠቀሱት የኦሮሚያ፤ የአማራ፤ የትግራይ፤ የጋምቤላ፤ የቤኒሻንጉልና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር አብቃይ በሆኑና ዘር መዝራት ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች ለዘር ምቹ እንደሚሆን ይገመታል፡፡

አስቀድሞ የተሻለ እርጥበት በነበራቸውና ዘር መዝራት በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በመብቀል ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ለሰብሎቹ ጤናማ እድገት መልካም ሁኔታ እንደሚፈጥር ይገመታል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከመደበኛው በላይ የሆነ ዝናብ ማሳ ላይ በመንሳፈፍ በቡቃያ ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊው ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የማጠንፈፊያ ቦዮችንና የጎርፍ መከላከያ እርከኖችን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በአንፃሩ በመደበኛ ሁኔታቸው የእርጥበት እጥረት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች በቂ ዝግጅት በማድረግ የሚገኘውን እርጥበት በሰብል ማሳዎች ላይ እንዲቆይ ማድረግና በተጨማሪም ከማሳ ውጪ የውኃ ማሰባሰብ ስራዎች ትኩረት እንዲያገኙ ይመከራል፡፡ እንደሚታወቀው እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች በተለየ መልኩ በሰብል ተባዮችና በሽታ የሚጠቁ እንደመሆናቸው በተለይም ዘር ገና ባልተዘራባቸው ቦታዎች ከአስተራረስ ጀምሮ እስከዘር መረጣ ድረስ አስቀድሞ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል፡፡በአንዳንድ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የመጠጥ ውኃ አቅርቦትንና የልምላሜ ሁኔታውን እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ የሚገኘውን ውኃ በጥንቃቄ መያዝና በተለያየ መልኩ ከሚከሰት ብክነት መከላከል ያስፈልጋል፡፡ በትንበያው ደረቅ ሆነው እንደሚቀጥሉ በተጠቆሙ አካባቢዎች አማራጭ መፍትሄዎችን ከወዲሁ ሊመለከቱ ያስፈልጋል፡፡

## <u>እ.ኤ.አ ከጁን 21-30/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>
## <u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ውስጥ የክረምቱ እርጥበታማ ሁኔታ በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ እየተሰፋፋ በመሄድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚስተዋል ትንበያው ያመለክታል።

ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ተከዜ፣ የላይኛው አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው የገናሌዳዋ እና የላይኛውና መካከለኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ሊኖራቸው ይችላል። በተጨማሪም የአዋሽና የአባይ ምስራቃዊው ክፍል ተዋሳኝ ተፋሰሶችና ጥቂት የመካከለኛው አዋሽና የላይኛው ተከዜ እንዲሁም የአፋር ደናከል ተዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የመሬት ሽፋኑ የሳሳ በመሆኑ አልፍ አልፎ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።